


# «ክቡር ሞቱ - ለሰማዕቱ»!



(ለአረጋዊ ገብረዮሐንስ)

ይድረስ ለወንድሜ ለትግራዩ፣
ከሰማዕታት መንደር ከሰማዩ፤

በጥርጣሬ ዐይነ-ህሊና - አጮልቄ እያየሁህ፣
በዝምታህ ግራ ገብቶኝ - ከሩቅ አምባ ለታዘብኩህ፤
በሕይወትህ ክቡር ዋጋ - ማንነትህን አሳየኸኝ፤
ማን ነኝና ልገምትህ - ካሁን ወዲያስ አፍም የለኝ::
እምታዋየው ወገን ስትሻ - በብረት አጥር ከልለውህ፣
ባፈ-ጮሌ ከርሳም ካድሬ - የፕሮፓጋንዳ መርዝ ረጭተውህ፣
እንደ ረመጥ የፍም እሳት - በተዳፈነ ትኩሳት፣
ስትለበለብ ስትከስል - መኖርህን መች አወኩት?

ይድረስ ላገሬ ልጅ ጦማር - ለአንድ አፍታ፣
ከሰማየ-ሰማያት ጥግ - ለምትኖረው በእፎይታ፤

ተወጣኸው አንተስ ከፍለህ - የትውልዱን ቀሪ ፍዳ፣
ይብላኝ ለሱ ለቀረበት - ለሚሰቃይ በደም ዕዳ፤
ባረመኔ ድርጊቱ - በጭካኔው ሳይፀፀት፣
«መሸታ ቤት በጸብ ሞተ..» - ብሎ አናፋ ዳግም ምጸት፤
ደምህ ደመ-ከልብ ሆኖ ሳይቀር - ልቡ ሲያውቀው፣
ሲያቃዠው ነው! እንቅልፍ ነስቶ ሲያባንነው!

ይድረስ ለናቴ ልጅ  - የእምዬ የኢትዮጵያ፣
ካለህበት የዕረፍት ሥፍራ - ሰላም ይሁን ሃሌ ሉያ!

በተምሣሌት አርዓያ - በነጻነት ምኩራብ ማማ፣
በሕይወትህ ኀልፈት ግብር - የለኮስከው ብርሃን ሻማ፣
በቀቢፃን ቁራጭ ትንፋሽ - እንኳን ባፍታ እፍ---ታ፣
ውሽንፍሩ.. ውዥንብሩ.. - አውሎ ነፋስ ቢበረታ፣
ከቶ አይጠፋም ለዝንተ-ዓለም፣
ደምቆ ይበራል በእናት አለም!
ለስጦታህ ታላቅ ጸጋ!
ዕሴት ዕንቁ ክቡር ዋጋ!
ሰላም.. ፍትህ.. እንዲያብቡ - ለከፈልከው መስዋዕትነት፣
ክበር በላይ! «ክቡር ሞቱ»! ለሰማዕት!!

**ጌታቸው አበራ**
**ሚያዚያ 2002 ዓ/ም**
**(ኤፕሪል 2010)**